# የገዢዎቻችን ክንድ ሲጠነክር እንዲህ ብለን እንፀልይ!

አቤቱ ይቅር ባይ አባታችን ሆይ አንተን እናመልካለን:: የተደረገብንን አስብ ተመልከትም፥ ስድባችንን እይ እርስታችንንም ለእንግዶች ቤቶቻችንም ለሌሎች ሆነ::
የገዢዎቻችን ክንድ በኛ ላይ ፈርጥሞ ደሀ አደጎችና አባት የሌለን ሆነናል::
እናቶቻችን እንደመበለቶች ሆነዋልና አትርሳን:: የምድራችንን ዉኃ በገንዘብ ገዝተን ጠጣን እንጨታችንንም በዋጋ ገዛን:: ገዥዎቻችን በአንገታችን ላይ ቆመዉ መተንፈስ አቅቶናል:: እኛ ደክመናል እረፍትም አጥተናል የምድራችንን ፍሬ በሰላም ብልተን እንጠግብ ዘንድ ፈቃድህ ይሁንልን::
ይቅር ባይ አባታችን ሆይ ከፅኑ ረሃብና መከራ የተነሳ ገፆቻችን እንደምድጃ ጠቆሩ ፊታችንም ጎሰቆለ:: ሳናጣ ያጣን ሳንጣላ የተለያየን የአህዛብ መሳለቂያ የክስረትና የዉድቀት ምሳሌ ሆነናል እና ጉልብት ሁነን::
ሽማግሌዎቻችንን በአደባባይ አዋረዷቸዉ:: ጎልማሶቻችንንም ከክብራቸው ሻሯቸዉ ከደረሰብን ግፍም የተነሳ የልባችን ደስታ ተሰርቋል ወደልቅሶም ተቀይሯል::
በገዢዎቻችን ፈርጣማ ክንድ ባገኘን ጽኑ ስቃይ ልባችን ታሟል፥ **ስለምን ለዘላልም ትረሳናለህ? ስለምንስ ለረጅም ዘመን ተውከን?**
ይቅር ባይ አባታችን ሆይ በፊትህ ተንበርክከን በደላችንን ይቅር በለን ብለን እንማፀንሃለን። አቤቱ ወደአንተ መልሰን እኛም እንመለሳለን ቀሪ ዘመናችንን አድስልን። የማዳንህን ስራ አድርግልን፥ እንባችንን አብስ፥ ነጻነታችንን ስጠን፤ ከገዢዎቻችን ክፉ ስራ ዛቻና ፉከራ አድነን፥ ከነእርሱ ትእቢት የተነሳም ስጋችንን ከመታወክ እምሮአችንንም ከእረፍት ማጣት አድን፥ የመከራዉን አገዛዝ መሸከም አቅቶናልና አንተ ኃይል ሆነህ ከስቃይ ሁሉ አዉጣን።
**በቅድስቲቱ ሃገራችን ኢትዮጵያ ሁላችንም በአንድነት፥ በፍቅር እና በመከባበር እንድንኖር ፍቀርህንና ሰላምህን ስጠን አሜን!**

ፍቀር ነኝ ከአዲስ አበባ
**ethio.fikir@yahoo.com**